# ክርስትና በጊዜ ባቡር

በዓለማችን የጊዜ ቀመር ከክርስቶስ ልደት በፊትና በኋላ ብለን እንደምንቆጥር ሁሉ፥ እርሱ በተገኘበት ስፍራ እንደነበረ የሚቆይ ታሪክ ካለመኖሩ የተነሳ፥ በግል ሕይወታችንም ከክርስቶስ በፊትና በኋላ እንላለን።

ክርስትና እምነት ሆኖ ከተደራጀና ቤተክርስቲያንም ከተመሠረተች ሁለት ሺህ ዓመታት ተቆጠሩ። እነዚህን ዓመታት በተከታታይ በሚቀርቡ ጹሑፎች እንቃኛለን። ታሪኩን በቅጡ ለመመልከት እንዲረዳን ተከታታይነቱን እየጠበቅን የጊዜ እርከን ለማበጀት ታሪኩን እንደ ባለሰባት ክፍል (ፉርጎ) ባቡር አድርግን እያንዳንዱን ጊዜ እንደ አንድ ክፍል ለመመልከት እንሞክራለን።

ዓላማችንን ከተረዳን እስኪ ወደ መጀመሪያው ክፍል እንግባ። እያንዳንዱ ክፍል ራሱን የቻለ የጊዜ ወቅት ስለሆነ፣ ስለቤተክርስቲያን የሚተርከው ታሪክ፥ የሚሰጠው ምስክርነት የሚገልፀው ዕውነት አለው።

የመጀመሪያው ክፍል ወይም የታሪክ እርከን የክርስቶስና የበጉ ሐዋርያት ዘመን ተብሎ ይታወቃል።

ጊዜው ከክርስቶስ ልደት እስከ 70 ዓ.ም. ሲሆን የምስክርነቱ ጮራ የፈነጠቀበትና የተሻለ መንገድ መኖሩ የታወጀበት ጊዜ ነበር። ከእምነት እድሜ ቆጠራ አንጻር ሲታይ የክርስትና እምነት የሁለት ሺህ ዓመት እድሜ ወጣት ይመስላል። ክርስትና ግን ሥር ያለው እምነት ነው። ስሩ ደግሞ ከክርስቶስ ልደት አልፎ በአይሁድ ታሪክ ውስጥ የተመሠረተ ነው። ክርስትና ከነቢያት በፊት ስር ያለው፤ ከነዳዊት በፊት፣ ከነሙሴ በፊት፣ ከነአብርሃም በፊት እስከ መጽሐፍ ቅዱሳችን መጀመሪያ ገጾች የሚደርስ አንጋፋ እምነት ነው።

የዛሬ ሁለት ሺ አመት ግን አንድ ነገር ሆነ። በአንዲት ቤተልሔም በምትባል የይሁዳ መንደር፤ ወንድ ልጅ ተወለደ። ከዚያም የተነሳ የአለም ታሪክ ለዘለአለም ተለወጠ።

ይህ ወንድ ልጅ ሰውም አምላክም የሆነው የናዝሬቱ ኢየሱስ ነው። በትምህርቱ አዲስ እንቅስቃሴ ጀመረ። ፀንቶ የኖረውን ወግና ልማድ አናጋ።

አዲስ ቀን ጠባ፥ አዲስ የእምነት ጮራ ፈነጠቀ። ጥቂቶች ብቻ ተከተሉት። ለብዙዎች ግን አልዋጥላቸው አለ። እንዲያውም የእምነት መሪዎችንና ባለሥልጣኖችን አስቆጣ።

ስለዚህ ይህንን አዲስ እንቅስቃሴ ላንዴና ለዘለአለም ለመቅጨት ተስማሙ። የእምነቱን ጀማሪና መምህር አይቀጡ ቅጣት እንቅጣው ብለው በመስቀል ሰቀሉት፥ ገደሉት። ቀበሩት። እርሱ ግን አምላክ ነውና ሞትን አሸንፎ ተነሣ። ይህ ክስተት ለአዲሱ እንቅስቃሴ አዲስ ጉልበት ሰጠው። ይህ እምነት እንደ ሰደድ እሳት በመያያዝ አካባቢውን ሁሉ አቀጣጠለው። የተቀጣጠለው እሳት ደግሞ በሩቅ የሚታይ ብርሃን ሆነ።

ይህንን ብርሃን ለሌሎች ለማሳየት እነኚያ ጥቂት ተከታዮቹ ሕይወታቸውን እንኳ እንደ ዋጋ ለመክፈል ወደኋላ አላሉም። በጊዜው የነበሩ የእምነትና የልማድ መሪዎች ይህን አዲስ የወይን ጠጅ በአሮጌ ማስቀመጫ ለመያዝ ሞከሩ፣ ማስቀመጫው ፈነዳ! ወይን ጠጁም ፈሰሰ እስከ ዛሬም ድረስ ደረሰ።

የዚህ ክፍል ዘመን ተጠቃሾች ጳውሎስ የሚሉት ቀንደኛ ፈሪሳዊ ጴጥሮስ የሚሉት አሳ አጥማጅ፣ ዮሐንስ የሚሉት ለስልሳ ሰውና በጣት የሚቆጠሩ ሴቶችና ወንዶች ናቸው። ታሪክ ሳይጠቅሳቸው ታሪክን የሰሩ።

የመጀመሪያው ክፍል እንግዲህ ከክርስቶስ መወለድ አንስቶ ክርስትና የስደት ሰለባ እስከሆነችበት ጊዜ ያሉት ሰባ ዓመታት መሆናቸው ነው።

ይህንን ክፍል ከቃኘን እስኪ ወደ ሁለተኛው ፉርጎ እንግባ። በዚህ በሁለተኛው ክፍል ያለው የባቡሩ እንቅስቃሴ ንቅናቄ የበዛበት ስለሆነ ቀበቷችንን ጠበቅ ማድረግ ያስፈልገናል።

ይህ ሁለተኛ ክፍል የካቶሊክ ወይም አለም አቀፍ ክፍልና ዘመን በመባል የሚታወቅ ሲሆን (ይህ ቃል በዘመናችን የምናውቀውን የካቶሊክ ቤተ እምነት የሚያመለክት አይደለም።) ከ70 እስከ 312 ዓ.ም. ድረስ የቆየ ነበር። ይህ ወቅት ክርስትና በመከራ የተፈተነበት፤ ሆኖም ከችግርና ከመከራ በላይ መሆኑን ያስመሰከረበት ዘመን ነበር።

ክርስትና ከአይሁድ እምነት የወጣ ኑፋቄ (CULT) ሳይሆን የሌሎችንም እምነቶች ዕውነት የሚጠይቅ ከመሆኑ የተነሣ "ካቶሊክ" ወይም "አለም አቀፍ" የሚለውን ስም አገኘ። ዘመኑ ያንን የተቀጣጠለ ሰደድ እሳት ለማጥፋት ዓለም "ክተት ሠራዊት ምታ ነጋሪት" ብላ የዘመተችበት ጊዜ ነበር።

በዚያው መጠን ደግሞ አማኞች ከተቀበልነው እውነት "ወይ ፍንክች... ወይ ንቅንቅ!" ብለው በቆራጥነት አንበገርም ያሉበት ዘመንም ነበር። ከየትኛውም ዘመን ይልቅ የዚህ ዘመን ታሪከኞች ሰማዕታት ናቸው። ለእምነታቸው ሲሉ መስዋዕት የሆኑ ተራ ሰዎች። በዚህ ዘመን የተፈጸመን አንድ እውነተኛ ታሪክ ስንመረምር የዘመኑን ሁኔታ ለመመልከት ይረዳናል።

የታሪኩ ባለቤት ፖሊካርፕ የተባለ ሰው ሲሆን፥ (በቤተክርስቲያን ታሪክ ውስጥ የታወቀ ነው።) ሁለተኛ ትውልድ ደቀ መዝሙር ነበር። የደቀ መዝሙሩ የዮሐንስ ተማሪ በሰምርኔስ የምትገኛዋ ቤተክርስቲያን መጋቢ (ፓስተር) ነበር የሚባለው ይህ ሰው፥ በእድሜው የ86 ዓመት ሰው ነበር። በሰዎች ዘንድ የተከበረና የተወደደ ሰው ነበር። ክርስቲያኖችን ይዞ ማሰር የጊዜው ልማድ ስለነበረ ባለሥልጣናት አስረውት ብዙ ሕዝብ ወደተሰበሰበበት ስታዲየም አመጡት።

በጊዜው ክርስቲያኖች እየተያዙ ሕዝብ በተሰበሰበበት ሥፍራ በአራዊት እንዲበሉ ማድረግ ከመዝናኛ ፕሮገራሞች አንዱ እንደ ነበረ ታሪክ ይመሰክራል።

አገር ገዢው ግን ፖሊካርፕን ከመቅጣት ይልቅ ሕዝብ በተሰበሰበበት ቦታ የቀረበበትን ክስ እንዲክድ ለመነው። ክሱ "ፖሊካርፕ ክርስቲያን ነው።" የሚል ነበር። አገረ ገዢው ጠጋ ብሎ፥ "ፖሊካርፕ ሆይ! በቄሳር ስም ብትምል ብቻ በነጻ ትለቀቃለህ።" አለው። ፖሊካርፕ ግን "እኔ ክርስቲያን ነኝ፣ በቄሳር አልምልም። " አለው። አገረ ገዢው፥ "እባክህ በሕዝቡ ፊት አንዴ ብቻ በቄሳር ስም ማል።" ሲል ጠየቀው። ፖሊካርፕ ግን "ለሕዝቡም ለአንተም መልሴ አንድ ነው። እኔ ክርስቲያን ነኝ።" ሲል መለሰለት። አገር ገዢውም "አሻፈረኝ ካልክ አናብስቱን እለቅብሃለሁ።" ሲል ማስፈራራቱን ቀጠለ። ፖሊካርፕ ግን "ልቀቃቸውና ይምጡ የአንተ አናብስት አያስፈሩኝም።" ብሎ መለሰለት።

አገረ ገዢው "በአናብስቱ የምታላግጥ ከሆነ በሣት አቃጥልሃለሁ።" በማለት ሊያስፈራራው ሞከረ። ፖሊካርፕ ግን፥ "አሁን ነዶ በጥቂት ጊዜ ለሚጠፋ እሳት ከዘላለም እሳት ያዳነኝን ጌታ ብክደው ለሮምም፣ ለቄሳርም የማልጠቅም ዜጋ እሆናለሁ።" በማለት አሻፈረኝ አለ።

አገር ጊዢው ድምጹን ከፍ አድርጎ ለሕዝቡ፥ "ፖሊካርፕ ክርስቲያን ነኝ ይላል።" በማለት አሳወቀ። ህዝቡም፥ "ይህ ድፍን እስያን ያሳተ ነው፤ ይህ የክርስቲያኖች አባት ነው። ይህ አማልክቶቻችንን ሁሉ ያጠፋ ነው።" በማለት አወገዙት። ከዚህ ምልልስ በኋላ ተቃጥሎ መስዋዕት ሆነ። ይህ የአንድ ሰው ታሪክ ነው። ነገር ግን በዚህ ዘመን ያለፉ የብዙ ሰማዕታት ታሪክ ተመሳሳይ ነው። የቤተክርስቲያን ታሪክ በእንዲህ አይነት ሰዎች ደም የተጻፈ ነው። በሚቀጥለው እትም ወደ ሦስተኛው የባቡሩ ክፍል ገብተን እናያለን።

ክርስትና የመንግሥት ሥልጣን የያዘበት ዘመን። ጊዜው ከ312 እስከ 1517 ዓ.ም. ምስክርነት የክርስትና መሠረት እምነት (ዶክትሪን) ተፈትኖ የጠራበት የእምነት አንቀጽ በጉባኤ የረቀቀበት ይህ ዘመን የብዙ ታሪከኞች ዘመን ነው። ከሁሉም በላይ ጐልቶ የሚታየው ግን "ንጉሥ" ነበረ። ዘመኑ ክርስትና ከካታኮንብ የመደበቂያ ዋሻና ተመሳሳይ መደበቂያዎች ወጥቶ በሥልጣንና በክብሬታ ስፍራ የተቀመጠበት ዘመን ስለነበረ፥ ክርስቲያኖች የጠፉ መሰሎ ነበር። ወሬያቸውም ስማቸውም እየተረሳ ነበር።

በዚህ ጊዜ ነው ቄሳሩ መኳንንቶቹንና የጦር አለቆቹን ሰብስቦ "መርዛማ የሆነውን የክርስትናን እምነት ታላቂቷ ሮም ስላጠፋች ደስ ይበለን።" ብሎ ፌሽታ ያደረገው። በደስታም በወርቅ ዋንጫ የወይን ጠጅን በመጠጣት የክርስትናና መጥፋት አከበሩ ይባላል።

በውጪ ሲታይ የእምነት ድል የሚመስለው ይህ ሁኔታ የክርስትናን እምነት ያሳነፈው፣ ያዘናጋውና ወደ ውድቀት ያደረሰው ነበር። ያ ብቻ ሳይሆን መከፋፈል በቤተክርስቲያን እንዲመጣም አደረገ። ከውጪ የሚገፋትና የሚያጠቃት ኃይል ከሌለ እርስ በርስ መፋተግና መባላላት የቤተክርስቲያን የረጂም ጊዜ ታሪክ ነው።

ከዚህ መጐሻሸም ጋር የእምነት መሠረተ ትምህርትም እየተናጋ መጣ። ሁኔታውን ለመረዳት በዘመኑ የተፈጸመ የአንድ ሰው ታሪክ እንመለከት። የዚህ ሰው ስም ኤርየስ (በአማርኛ አርዮስ የተባለው) ነው።

ጳጳስ ኤርየስ በጊዜው በጣም የታወቀ የቤተክርስቲያን ሰው ነበር ይባላል። ጐበዝ ተናጋሪ፣ አንደበተ ርቱዕ፣ ቀና መንፈስ ያለው፣ በደረሰበት ሁሉ መልካም አቀባበል የሚያገኝ ሰው ነበር። በብዙ ገዳማት እየዞረ በማስተማሩ መልካም ስምና ብዙ ተከታይ ያፈራ ሰው ነበር።

የኤርየስ ትምህርት ግን እየተለወጠ ቆይቶም እየተበላሸ መጣ። በኋላም ክርስቶስ ከተፈጠሩ ፍጥረቶች ሁሉ የበላይ ነው እንጂ አምላክ አይደለም የሚለውን የተሳሳተ አሳብ የትምህርቱ ዋናና መካከለኛ ክፍል አደረገው።

ይህ ሰው ሳይታሰብ ብዙ ተከታዮች አፈራ። ቤተክርስቲያን የእርሱን ትምህርት ለመቃወም በወሰነችበት ጊዜ እርሱ ባለብዙ ተከታዮች ሆኖ ነበር። በብዙ ቦታዎች ክርስቲያኖች ሲገናኙ ወጤቱ መከራከርና መበጣበጥ ሆነ።

መለያየቱንና መበጣበጡ እየበዛ ስለሄደ ልዩነቱን ለማጥበብና ስምምነት ለመፍጠር በንጉሥ ቆንጠስጢኖስ መሪነት የመጀመሪያው የኒቂያ ጉባኤ ላይ በ325 ዓ.ም. ተሰየመ። በዚህ ጉባኤ ላይ ከክርክሩ መክረር የተነሣ ሰዎች ስሜታቸውን መቆጣጠር ያቅታቸው ነበር።

ተናጋሪን እንዳይሰማ ማድረግ አሳቡን ሳይጨርስ በማንጓጠጥ ማቋረጥ በአእምሮ ሳይሆን በስሜት ሰው እንዲመራ ማደረግ የጉባኤውን ዓላማ ወደማሳት ስለደረሰ ንጉሡ ራሱ በተደጋጋሚ መጥቶ ሥርዓትን ያስጠብቅ ነበር።

በኋላ እንዲያውም የንጉሡ መገኘት አስፈላጊ ስለነበር የስብሰባው ሊቀመንበር ሆኖ መርቶአል። ክርክሩ እየተራዘመ ሲሄድ ግን ይህ በንግግሩ ተወዳዳሪ የማይገኝለት ጠንቀኛ መነኩሴ (ኤረየስ) ክርክሩን አያሸነፈ መጣ።

ተቃዋሚዎቹም እርሱን የሚወዳደር መልስ በማጣታቸው ግራ ተጋቡ። አንዳንዶቹ እንዲውም "ምናልባት ይህ ሰው ትክክል ይሆንን?" በማለት መጠራጠር ጀመሩ።

በዚህ ጊዜ ነበር አንድ ከግብፅ ምድረ በዳ የመጣ ባሕታዊ መነኩሴ፥ ሰሙና አድራሻው ያልታወቀ ሰው ከተቀመጠበት ዘሎ ተነስቶ ወደ ጉባኤው መካከል የገባው።

ከዚያም ለብሶት የነበረውን የቆዳ ልብስ መቅደድ ጀመረ። ጉባኤውም በመደናገጥ ፀጥ ብሎ ይመለከተው ጀመር። በልዩ ኃይል እንደ ተገደዱ የጉባኤው ዓይንም አሳብም በዚህ ሰው ላይ ወደቀ። ሰውየውም ልብሱን ቀዶ በጠባሳ የተሞላ ጀርባውን አሳያቸው።

ለጌታ ሲል የደረሰበት ግርፋት የተወውን ጠባሳ። ከጥቂት አመታት በፊት የቄሳርን መኳንንትና አለቆች ለማዝናናት በአራዊት መካከል ተጥሎ በአራዊት ጥፍር የተቧጠጠውን ገላውን አሳያቸው። ሰውነቱ የሰው ሰውነት አይመስልም ነበር።

ጮክ ብሎ ሲቃ ይዞት በሚንቀጠቀጥ ድምፅ "ይህ ለጌታዬና ለአምላኬ ለኢየሱስ ክርስቶስ በመቆሜ የተቀበልኩት ግርፋት ነው። ይህ ለእኔ የክብር ማሕተሜ ነው። ይህ ለእኔ ጌጤ ነው። ይህንን ጠባሳ ስቀበል ግን ግርፋቱ በጣም ያም ነበር። ያውሬዎቹ ጥፍር ያንገበግብ ነበር። በሥቃይና በመከራ ነው ይህንን ሁኔታ ያለፍኩት። ነገር ግን የዚያን ጊዜ ከተሰማኝ ህመምና ስቃይ የበለጠ ዛሬ እናንተ አምላኬን አምላክ አይደለም ብላችሁ ስትሳደቡ መስማቴ የበለጠ ያማል፣ የበለጠ ይጐዳል።

ከዚያ በኋላ የተናገረውን ንግግር ከምድረበዳ የመጣ ያልተማረ ሰው ሊናገረው የሚችል አይነት ባለመሆኑ ጉባኤው "መንፈስ ቅዱስ ወደ እውነት ሊመራን በዚህ ሰው ተናገረን።" ብለው በእንባና በንስሃ ተቀበሉት። ኤርየስና ከተከታዮቹ አንዳንዶቹ ከያዝነው ትምህርት አንመለስም ብለው እምቢ ስላሉ፥ ጉባኤው አወገዛቸው።

ከዚያ ጊዜ ጀምሮ አገልጋይ ወይም መሪ እምነትን የሚያሳስት ትምህርት ሲያስተምርና አልመለስም ብሎ እምቢ ሲል ቤተክርስቲያን "እንደ ኤርየስ የተወገዝክ ሁን" … "ውጉዝ ከመ አርዮስ" ብላ ታወግዛለች።

የኒቂያ ጉባኤም እስከ ዛሬ ድረስ በቤተክርስቲያን የፀናውን የእምነት ኑዛዜ (Creed) አርቅቆ ተበተነ። የቤተክርስቲያን ታሪክ እንደዚህ ባሉ ስማቸውና ማንነታቸው ያልታወቀ ሰዎች ታሪክ ነው። ሌላው ቢዚህ ዘመን የተፈጸመውና ሊጠቀስ የሚገባው ታሪክ የታላቂቷ ሮም ውድቀት ነው። በ410 ዓ.ም. ታላቂቷ ሮም ወደቀች። በውበቷ አለምን ሁሉ መርዛ ሱሰኛ አድርጋ የያዘቸው ሮም፣ ክርስትናን ከአለም ላይ አጠፋሁ ብላ በዓል ያከበረችው ሮም ሳይታሰብ ድንገት ወደቀች።

ሮም ስትወድቅ ደግሞ አለም ራሷ ተንገዳገደች፣ ተብረከረከች። ምክንያቱም ሮም እንደተራመደች አለም ትራመድ ነበር። ሮም ስተመራ ያለጥያቄ ትከተል ነበር። "ሮም ካሰነጠሳት አለም ጉንፋን ይይዛታል።" እያሉ ነበር ሮማውያን የሚኩራሩት "መንዶች ሁሉ ወደ ሮም ያደርሳሉ።" ሲባል ባህሎችና ወጐች የሮምን ጠባይ ያንፀባርቃሉ ማለት ነበር። "የከታማዎች ልዕልት" የተባለችው ሮም ተይዛ ስትዘረፍ ያየ ሮማዊ፥ ልጃገረድ ልጁ በወንበዴዎች ተይዛ የተደፈረቸውን አይነት ሃዘን አዘነ። ሴቶች ልጆች ብቻ ሳይሆኑ ወንዶችም በአደባባይ ድምጻቸውን ከፍ አድርገው አለቀሱ። ጀሮም የተባለው ታዋቂ ሮማዊ ታሪክ ፀሐፊ ስለዚህ ጊዜ ሲጽፍ "አለምን ሁሉ ይዛ የነበረችው ሮም ራሷ ስትያዝ ለመናገር ፈልጌ አፌን ብከፍት ድምጼ ከጎሮሮዬ ተጣብቆ ቀረ፤ ሮም ከሌለች ምን ድምፅ አለኝ?" ብሏል። ታዲያ የሮም መውደቅ ከክርስትና ታሪክ ጋር ምን ግንኙነት አለው?

ኩሩ የነበሩት ሮማውያን ከወደቀባቸው ከዚህ ድንጋጤ ሲነቁ የሚያዩትን ማመን አቃታቸው። ብዙ ጥያቄ መጠየቅ አመጡ። "ይህ ቁጣ የመጣብን አማልክቶቻችን ተቆጥተው ነው" አሉ። መሪዎቻችን ሳንወድ የክርስትናን እምነት እንድንቀበል ስላደረጉን አማልክት ተቆጥተው ያመጡብን መዓት ነው ብለው በክርስትና እምነት ላይ ተነሡ።

በሌላ በኩል ደግሞ ወራሪው ክርስቲያን ነኝ ባይ ስለነበር ከተማዋ ስትዘረፍ ቤተክርስቲያን እንዳትነካ ስላደረገ ቤተክርስቲያን የወራሪው አበር ስለመሰለች በጥላቻ ትታይ ጀመር።

ብዙ ጥያቆዎች ተነሱ! በመንገድ ጥያቄ፣ በአደባባይ ጥያቄ፣ በቤት ጥያቄ፣ በውጭ ጥያቄ፣ ሰለእምነት ጥያቄ፣ ስለቤተክርስቲያን ጥያቄ ሮማውያንና የሮም ተከታዮች በጊዜው አንገብጋቢ የሆኑ ብዙ ጥያቄዎች እንደ ቁስል የሚጠዘጥዙ ጥያቄዎች በክርስትና እምነት ላይ አስነሱ። ለእነኚህ ጥያቄዎች መልስ የሚሰጥ ሰው ታዳያ እግዚአብሔር አስነሳ። ኤሆልየስ አውግስጦስ።

- ኤሆልየስ አውግስጦስ (St. Augustin) በመባል የታወቀው የሂታ (ሰሜን አፍሪካ) መጋቢ ጨለማ ለሆኑት ለእነኚህ ቀናቶች ብርሃን ማሳየት ጀመረ።
- የዚህ ሰው ትምህርት ለዚያ ዘመን ብቻ ሳይሆን እስከ ዛሬ ድረስ በቤተክርስቲያን ለሚነሱ ብዙ ጥያቄዎች መልስ ሆኗል። የቤተክርስቲያን ታሪክ እግዚአብሔር ባስነሳቸው ጊዜና ባስቀመጣቸው ቦታ ታማኞች በሆኑ የተሞላ ነው።
- ሌላው የሮም ውድቀት ውጤት በሕግ የሚተዳደርና ዕውቀት የሚፈልግ ሥርዓት መቋቋሙ ነው። ይህ ሥርዓት በአጠቃላይ አውሮፓ ተብሎ ይታወቃል።
- ይህ ሥርዓት በተቋቋመበት ሥፍራ ሁሉ መሪዎች የቤተክርስቲያን ሰዎች ነበሩ። ሥርአቱ በተቋቋመበት ቦታ ሁሉ ጳጳሳትና የቤተክርስቲያን መሪዎች የሥልጣን ተካፋዮች ነበሩ።
- ከዚህም የተነሣ ቤተክርስቲያን አለምን መለወጥ ስላልቻለች አለምን መሰለች።
- በወንጌል ያልተለወጠውን በኃይል ለመለወጥ ዘመቻና አዋጅ በዛ።
- ቅድስት አገርን ከወራሪ እስላሞች ለማስለቀቅ ብዙ ጦርነቶችን መራች (CRUSADES)
- ይህ ዘመን የቤተክርስቲያን የጨለማ ዘመን ተብሎ ይታወቃል።
- ከእምነት አንጻርም ብዙ አጠያያቂ የሆኑ ልምምዶች በቤተክርስቲያን የተወረሱት በዚህ ዘመን ነው።
- በዚህ በጨለማ ዘመን እግዚአብሔር ብርሃን ያደረጋቸው ሁለት ዮሐንሶች ጆን ዋይ ክሊፍና ጆን ሀስ - "የእግዚአብሔርን ቃል ተራው ምዕመን አንብቦ መረዳት ይችላል" የሚል በጊዜው ስርነቀል የሆነ ትምህርት አመጡ።

የሚቀጥለው ክፍል ብዙ ማየትና ማስተዋል የሚጠይቅ ስለሆነ ከመግባታችን በፊት መነፅራችንን እንወልውል።

1. የተሃድሶ ዘመን፥ ጊዜው_ከ1517 እስክ 1648 ዓ.ም.
   ምስክርነቱ፥ ክርስትና ወደቃሉ እውነት የተመለሰበት (Reformation)

ቤተክርስቲያን በመለያየት መስማማት መኖሩን ያወቀችበት (Denominations) በአስራ ስድስተኛው መቶ ክፍለ ዘመን የተሃድሶ መንፈስ የምዕራቡን ዓለም መልክ ጨርሶ ለወጠው። የቤተክርስቲያን ትምህርት ተሳስቷል፣ የጳጳሳቱም ሥልጣን አይገዛንም

የሚል አዲስ ኃይል አዲስ እንቅስቃሴ ተነሳ። በጀርመን ከታላቁ መሪያቸው ከማርቲን ሉተር የተነሳ "ሉተራን" ተብለው ሲጠሩ ቤተክርስቲያን ይህንን ሰው "በጓሮ ውስጥ የተለቀቀ ክፉ አውሬ።" ብላ አወገዘችው በመካከለኛ ግዛቶች (Sweeden, Norway, France) ከልምምዳቸው የተነሣ አነ ባፕቲስት (የዛሬ መጥምቃውያን) ተባሉ። በዳች ካሊቪኒስቶች …

ይህ እንቅስቃሴ እንግሊዝ አገር ደርሶ አንግሊካን ቸርች ሲመሠረት "በዘውዱ ላይ የመጣ እርግማን" ተባለ።

- በዚህ ዘመን ነው እስያና አሜሪካ ለመጀመሪያ ጊዜ በክርስትና እምነት የተጐበኙት።
- ክርስቲያኖችም ከክርክር ፀጉር ስንጠቃ ወደ ውቅያኖስ ስንጠቃ ተላለፉ።
- ወደሚቀጥለው ክፍል በአንድ ላይ እንሂድ? "ሞኙት ተላሊት" እያሉ የሚያሾፉባችሁ የገደል ማሚቶዎች አይጠፉም።

2. የእውቀት ዘመን
   ጊዜው፡ ከ1648 እስከ 1789
   ምስክርነቱ፡ ክርስትና ከአዋቂዎችና ከምሁራን የተወረወረባትን ቀስት የተቋቋመችበት

ክርስትና ያለድጋፍና ያለ ዕገዛ ብቻዋን መቆም እንደምትችል ያሣየችበት ሲሆን፣ ይሄኛው ዘመን የሚታወቅበት ሌላ ነገር ደግሞ በክህደት የተሞላ ዘመን መሆኑ ነበር። ሳይንስና የሰዎች አመለካከት የክርስትናን ቦታ ለውጦ ለምዕራባውያን ሥልጣኔና ባህል የመሠረት ድንጋይ ሆነ።

- ክርስትና ጊዜው ያለፈበት፤ ያረጀ ያፈጀ ለዘመኑ የሚሆን የሌለው የኋላ ቀርኞች ፈሊጥ ብቻ ተባለ።
- በዚያው መጠን ደግሞ ለክርስቲያኖች ክርስትና የማያወሩት ወሬ፣ የማያሳዩት ወግ ብቻ ሳይሆን የሚለማመዱት ልምምድ ሆነ።
- ክርስትና በመንግሥት ሳይደገፍ፣ በጳጳስ ስልጣን ሳይመራ በጉበዞች ጉልበት ተስፋ ሳያደርግ ብቻውን በወንጌል ላይ መቆም እንደሚችል አረጋገጠ።
- ሰዎችም በግፊትና በኃይለኞች በአዋጅ በመንግሥት ሳይሆን በስብከት ኃይል ብቻ እንደሚለወጡ እንደገና ተሰበከ
- በዚህ ዘመን ከተነሡ ሰዎች የሚታወስ ዮሐንስ ዌስሊ … አሁን ወደባቡሩ ኃይለኛ ክፍል ስንመጣ ስድስተኛ ፉርጐ እንገባለን።

3. የእድገት ዘመን
   ጊዜው፤ ከ1789 – 1914
   ምስክርነቱ፡ ክርስትና እውነትም ለአለም ሁሉ የሚደርስ እምነት - የሚሲዮናውያን አገልግሎት "ከእንግዲህ ይህ ዓለም ፍጹም ቤቴ አይደለም"

ይህ ዘመን ከመቼውም የበለጠ የቴክኖሎጂ እርምጃ የታየበት ነበር። ቤተክርስቲያንም ከየትኛውም ድርጅት የበለጠ የቴክኖሎጂ ውጤትን የተጠቀመችበት ዘመን ነበር።

- በተለይ የማተሚያ መኪና መሠራቱ መጽሐፍ ቅዱስን እያባዙ በሩቅ ለማድረስ ቅርብ መንገድ ሆነ።
- በየቦታው የተነሡ ሕዝባዊ እንቅስቃሴዎች - በተለይም የፈረንሳይ ሪቮሉሽን በዚህ ዘመን በክርስትና እምነት ላይ ተጨማሪ ተፅዕኖ Challenge አመጣ።
- በአንድ በኩል ቤተክርስቲያን የጨቋኙ መደብ ክፍል ናት ተብላ ስትነቀፍ በሌላ በኩል ደግሞ ማወቅ የማይገባቸውን በማሳወቅ "ንቃተ ሕሊና" በመስጠት የሕዝብ እንቅስቃሴ በማስነሳቷ ትወቀስ ጀመር።
- ጊዜውን ከምንም የበለጠ አንፀባረቂ የሚያደርገው ግን ሚሲዮናውያን በሩቅ ላሉ ወንጌልን ለማድረስ መጠራታቸውን ተቀብለው መነሳታቸው ነው። ወጋቸውን፣ ባህላቸውን አልፈው ወዳጆቻቸውን፣ ዘመዶቻቸው ትተው በሩቅ ላሉ በመስጠት ወጡ።
- ብዙዎች ለወንጌል ብለው ምቾታቸውን ትተው በሕይወታቸው ቆርጠው ወደማያውቁት ሕዝብና ባህል በመሄድ የወንጌል መልዕክተኞች ሆኑ።

ብዙ የሚጐዱ የሚያሙ ድንጋዮች ስለአሉ የራስ ቁር ማድረግ በዚህ ክፈል ውስጥ ይጠበቃል። ወደ ባቡሩ የመጨረሻ ክፍል ልንገባ ነው።

4. የተሻሻለው ዘመን

   ጊዜው፤ ከ1914 – 2000 ዓ.ም.
   ምስክርነት - ክርስትና የታሪክ ቅርስ ሳይሆን የሕዝብ ሂደት ክርስትና ወግና ባህል ብቻ ሳይሆን ከዚያም በላይ መሆኑ ተመሰከረ። ሃያኛው መቶ ክፍለ ዘመን ተንደርድሮ ግጭ ሲል ጥሩ መልክ አልነበረውም። እንዲያውም ከዘመናት ሁሉ አሥቀያሚ ፊት ያለው ነው።

የፖለተካና የጦር መሣሪያ እሽቅድምድም ተሻሻለ የተባለውን ሰው ኋላ ቀርነቱን አስመሰከረ። የፖለቲካ መለያየት፣ የዘርና የሃይማኖት ልዩነት፣ የቀለምና የፃታ ልዩነቶች ዓለምን አተራመሱ።

- ሁለት የአለም ጦርነቶች ብዙ ታላላቅ ጦርነቶች ቁጥር የሌላቸው ታናናሽ ጦርነቶች ዘመኑን የሚገልጡ ታሪኮች ሆኑ።
- አዋቂዎች በሃያኛው መቶ ክፍለ ዘመን አለም ያለ ጦርነት አንድ ቀን እንኳን አልዋለችም ይላሉ።
- ሕዝብ በሕዝብ ላይ፣ መንግሥት በመንግሥት ላይ፣ ሰው በሥልጣኔ ባደገ መጠን፤ በዕውቀት በተራቀቀ ቁጥር በቴክኖሎጂ በተሻሻለ ቁጥር ከውስጥ ግን ምንም እንዳልተለዋወጠ … እምነት የደካሞች ነው በማለት የተነሱት ኢምፔሪያሊስቶች፣ ኮሌኒያሊስቶች፣ ናዚስቶች፣ ፋሺሽቶች፣ ኮሚኒስቶች በዘመኑ የሐፍረት ግድግዳ ላይ የተጻፉ የዘመኑ አስቀያሚ ምልክቶች ሆኑ!

- ይህ ሁኔታ የፈጠረው የኤኮኖሚ አለመደላደል፣ የዘር ልዩነት አለመግባባት፣ የግለሰብ እኔ እበልጥ ውድድር መልስ የሌለው ብዙ ጥያቄ አስነሳ
- የአለም መንግሥታት መልስ እንሠጣለን ብለው ተሰበሰቡ፡፡ በመጀመሪያ League of Nations አንድ ጥያቄ እንኳን ሳይመልስ ፈረሰ፡፡
- አሁን ያለው United Nations ደግሞ አቅም ለሌላቸው ትንንሾች ብቻ የቦክስ መድረክ ሆነ፡፡
- ቤተክርስቲያን በዚህ ሁኔታ ለተፈጠረው ድብልቅልቅ ሳትታጠቅ ድንገት ደረሰባት መልስ አጣች፡፡ ግን አሁንም እንደሌላው ዘመን ሁሉ ክርስትና ያልታሰበ ሌላ ድል አገኘች፡፡
- ሦስተኛው ዓለም - በኢኮኖሚና በሥልጣኔ ኋላ ቀር የተባለው ሕዝብ ተኝቶ ይመስል ድንገት ነቃ፡፡ ተዳፍኖ እንዳደረ እሳት ትንሽ ሲቆሰቆስ መቀጣጠል ያዘ፡፡ እስያ ደቡብ አሜሪካና አፍሪካ የዘመኑ የእምነት ባለታሪኮች ሆነው ተነሡ።
- ታሪከኛዋ አውሮፓ ከደበታት የአለማመን እንቅልፍ መንቃት አቅቷት ቀና ስትል፣ ወጣት አሜሪካ በአቻ ጋብቻ ተይዛ ፓለቲካንና ክርስትናን ለማዋሃድ የቀድሞ ጳጳሳት በገቡበት ኩሬ ተንቦራጨከች።
- የእምነቱ ባላደራዎች ካልታሰበ ቦታ ተነሱ።

በዚህ ዘመን ቤተክርስቲያን የራቁትን የምታቀርብ የቀረቡትን ደግሞ የምታርቅ የሆነች ይመስላል። ይህ የክርስትና እምነት የሁለት ሺ ዓመት ምስክርነት ጨረፍታ ነው። በአንድ ፈጣን ባቡር በሰባት ልዩ ልዩ ክፍሎች። ክርስትና የብዙዎች ታሪክና የታሪክ ባለ ፀጋ ነች። ከሁሉም በላይ ክርስትና የኢየሱስ ጌትነት አዋጅ ነች፡፡